# ብሩሴሎሲስ

## ብሩሴሎሲስ ምንድን ነው?

ብሩሴሎሲስ ብዙ የተለያዩ እንስሶችን ለምሳሌ በግ፣ ፍየል፣ ከብት፣ አጋዘን፣ ትልቅ አጋዘን፣ አሳማ እና ውሾችን የሚያጠቃ በረቂቃን ነፍሳት ምክንያት የሚምጣ በሽታ ነው። ብሩሴሎሲስ ሰውንም ሊያጠቃ ይሚችል በሽታ ሲሆን ክጉንፋን በሽታ ጋር ተመሳሳይ ምልክቶች አሉት። ብሩሴሎሲስ ያለባቸው ሰዎች ትኩሳት፣ ላብ፣ ራስ ምታት፣ የጀርባ ሕመምና የሰውነት ድክመት ሊይዛቸው ይችላል። በሽታው ከጠና የመሃከለኛ የነርቭ ሲስተምንና የልብ ገበርን ሊጎዱ ይችላሉ። አንደኛው የበሽታው ዓይነት ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ እንደ ተደጋጋሚ ትኩሳት፣ የመጋጠሚያ ሕመምና ድካምን የመሳሰሉ ምልክቶች ሊያስከትል ይችላል። ምልክቶቹ ለበሽታው ከተጋለጡ ከአምስት እስከ ስልሳ ቀን በኋላ ሊታዩ ይችላሉ።



*የብሩሴሎሲስ ረቂቃን ነፍሳት*

የብሩሴሎሲስ ሰው ላይ መገኘት ይልተለመደ ሲሆን በአሜሪካን አገር ውስጥ በዓመት ከመቶ እስከ ሁለት መቶ ብቻ የታወቁ በሽተኞች ይገኛሉ። ብሩሴሎሲስ በጠና ሊያሳምም ቢችልም ሞት ማስከተሉ እምብዛም አይደለም።

## ሰው ብሩሴሎሲስ የሚይዘው እንዴት ነው?

ሰዎች የብሩሴሎሲስ ረቂቃን ነፍሳት ሊይዛቸው የሚችለው በሚከተሉት መንገዶች ነው

- ረቂቃን ነፍሳቱ የበከሉትን ነገር በመብላት ወይም በመጠጣት
- ረቂቃን ነፍሳቱን በመተንፈስ
- ቁስል ኖሮ በረቂቃን ነፍሳቱ ሲበከል

አብዛኛውን ጊዜ ሰዎቸ በሽታው የሚይዛቸው መንገድ ፓስተራይዝ ያልተደረገ የተበከለ ወተት ሲጠጡ ወይም አይብ ሲበሉ ነው። ረቂቃን ነፍሳቱን በመተንፈስም በሽታው ሊይዝ ይችላል። በዚህ መንገድ ብዙ ጊዜ ባይዝም የተወሰኑ ዓይነት ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ለዚህ ሊጋለጡ ይችላሉ - ለምሳሌ ቤተ ሙከራ ውስጥ ወይም ቄራ ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች። የተበከሉ ቁስሎች ለእንስሳት ሐኪሞች፣ ለቄራ ሠራተኞች ወይም ለአዳኞች ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ። አዳኞች ሳያውቁት የአደን አውሬ በሚያጸዱብት ጊዜ በብሩሴሎሲስ ረቂቃን ነፍሳት ተበክሎ ሲበሉት ሊይዛቸው ይችላል።

ረቂቃን ነፍሳቱን አውቆ አየር ውስጥ መልቀቅ ወይም ምግብ ውስጥ መክተትም ሰውን ሊያሳምም ይችላል።

## ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፍ ይችላል?

ብሩሴሎሲስ ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፍ ይችላል ሆኖም እምብዛም አይደለም። አልፎ አልፎ የሚያጠቡ እናቶች ጥቃቅን ነፍሳቱን ወደ ልጆቻቸው ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ረቂቃን ነፍሳቱ በግብረ ሥጋ ግንኙነትም ሊተላለፉ ይችላሉ።

## ብሩሴሎሲስ ሕክምና አለው?

ብሩሴሎሲስ በአንቲባዮቲክ ሊታከም ይችላል - ሆኖም ረጅም ጊዜ ሊፈጅና ሕክምናው ከባድ ሊሆን ይችላል። እንደ በሽታው ክብደትና ሕክምናው እንደተጀመረበት ጊዜ ለመዳን ከትንሽ ሳምንታት እስከ ትንሽ ወራት ሊፈጅ ይችላል።.

## ብሩሴሎሲስን መከላከል ይቻላል?

ብሩሴሎሲስ ክትባት የለውም። ሆኖም አስጊነቱን ለመቀነስ መንገድ ሲሄዱ ፓስተራይዝ ያልተደረገ ወተት፣ አይብ ወይም አይስ ክሪም አይጠጡ ወይም አይመገቡ። አዳኞች የእንስሶችን የውስጥ የሰውነት አካል ሲነኩ የላስቲክ የእጅ ጓንቲ ማድረግ አለባቸው።

## ብሩሴሎሲስ የሽብር የጦር መሣሪያ ሊሆን ይችላል የሚባለው ለምንድን ነው?

ብሪሴሎሲስ ሰውን አሳምሞ ከእለታዊ እንቅስቃሴ ለረጅም ጊዜ ሊያግድ ይችላል። ሰዎችን ለበሽታው በሚያጋልጥ መንገድ ረቂቃን ነፍሳቱን መልቀቅ ቀላል ነው። ለሞት ማድረሱ እምብዛም ቢሆን ብዙ

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Communications Office
625 North Robert Street/Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-4989
www.health.state.mn.us

ሰዎችን ሊያሳምም ይችላል። ብሩሴሎሲን ለይቶ አውቆ መከታተል ለሕዝብ ጤና ክፍል ከባድ ነው።

## ብሩሴሎሲስ የያዘኝ ከመሰለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

ብሩሴሎሲስ አለብኝ ብለው የሚያምኑ ሰዎች ዶክተር ጋር መሄድ አለባቸው። ከብሩሴሎሲስ ወይም ከማንኛውም ዓይነት ሌላ ከባድ በሽታ መራባት ጋር የተያያዘ ያልተለመደ ተግባር ከጠረጠሩ በአካባቢዎ ለሚገኘው የሕግ አስከባሪ ድርጅት ያስታውቁ።